እቅድና ግብ

በገርሃድ ኔህልስ

እቅድና ግብ

ብዙ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ስለ ብዙ ነገሮች ያልማሉ። አንዳንዶች ትንንሽ፥ ሌሎች ደግሞ ትልልቅ ዓላማ አላቸው። «ቅዳሜ ዕለት ወደ ሱቅ ሄደን ዕቃ እንገዛለን» ይህ ትንሽ ዓላማ ነው። «ዶክተር ለመሆን እፈልጋለሁ»፤ ይህ ደግሞ ተለቅ ያለ ነው። ዳሩ ግን ብዙዎቹ ትልልቅ የሕይወት ዓላማዎች ከግብ አይደርሱም። ለዚህም ምክንያቱ ከታለመባቸው በኋላ የሕይወት እቅድ፥ የመኖርያ ምክንያት ተደርገው ስለማይወሰዱ ነው።

ብዙውን ጊዜ ሕይወትን የሚያባክኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች የሕይወት እቅዶች ሆነው ይገኛሉ። ከእነዚህም የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች፡- ገንዘብ ማግኘት፥ ሕይወትን የሚያስደስቱ ነገሮች ማግኘት፥ መብላትና መጠጣት፥ መዝናኛና ስፖርት ጥቂቶቹ ናቸው። ከዚያም አንዳንድ ጊዜ ቆም ብለን ራሳችንን እንጠይቃለን፡- «የሕይወት እቅዱ ይኸው ብቻ ነውን? ለመብላት፥ ለመጠጣት፥ ለመዝናናት፥ ለመሥራት፥ ለማንቀላፋት ... ከዚያም ለመሞት?»

የማንኛውም መጣጥፍ (ጽሑፍ) እውነተኛ ዓላማ የሚወሰነው ቅርጹን በሚያወጣውና ይዘቱን (ዲዛይኔር) በሚያዘጋጀው፥ እንዲሁም ሥራውን በሚያከናውኑ ሰዎች ብቻ ነው። የሰውን ሕይወት የተመለከትን

እንደሆን ግን ይህንን የሚያደርገው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በእርግጥ ነገሮች ከመሠረታዊ ዓላማቸው ሊያፈነግጡ ይችላሉ። ለዳቦ መቁረጫ የተሰራው ቢላዋ፥ የነፍስ ማጥፊያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል። የአቶም ኃይል የተደላደለ ሕይወት አስተዋጽኦ የሚያደርግ የጉልበት (ኤነርጂ) ምንጭ የሆነውን ያህል፥ ማኅበረሰቡን ለማጥፋት ያገለግል ይሆናል፤ ተገልግለውበትማል። ከፈጣሪው በተተለመለት እቅድ ለመኖር የሚፈልግ ሰው፥ በሕይወቱ እውነተኛ ዓላማ አለው። ትርጉም ባለውና በእውነተኛ ዓላማ የሚኖረው የዚህ ዓይነቱ ሰው ነው፤ ብዙ ሰዎችም ይህን ይገነዘባሉ። እዚህ ላይ ሦስት ጥያቄዎችን ማንሳት ግድ ይሆናል። የእግዚአብሔር እቅድና የእኔ ዓላማዎች ባይስማሙ ምን ይሆናል? (አብዛኛዎቹ ሰዎች ለራሳቸው ፍላጎት በማድላት ይወስናሉ።) ሁለተኛው ችግር ደግሞ የበለጠ ስውር ነው። የእግዚአብሔር ዓላማና ግብ ለሕይወቴ ምን እንደሆን እንዴት አውቃለሁ?... ሦስተኛውም ራሳቸውን ከእግዚአብሔር እንደተሰጡ አድርገው ከሚያቀርቡት መጻሕፍት ውስጥ የትኛው ትክክልና ቅዱስ መጽሐፍ እንደሆን እንዴት እርግጠኛ መሆን እችላለሁ?

በዚህ ዓይነት ከሚወጡ ተከታታይ አነስተኛ መጽሐፍት መካከል በአንደኛው ውስጥ ይህ ጥያቄ በሚያሳምን መንገድ ተመልሷል። (መጽሐፉም ላለመደናገር ማወዳደር ማሰላሰል ማጠቃለል የሚል... ሲሆን

ከበስተጀርባው በሚገኘው አድራሻ ጠይቆ ማግኘት ይቻላል)።

ወንጌሉ ማለትም «የምሥራቹ» እግዚአብሔር ስለሰው ያለውን አመለካከት ያሳያል። ይህም በጣም ግራ የሚመስል ወይም አሉታዊ አመለካከት ሲሆን፥ ያለምክንያት ግን አልነበረም። ይህን በመራራ ልምምድ ውስጥ ተምረናል። ደግሞም ወንጌሉ ከመደናገር፥ ከመታለል፥ ከዓላማ ቢስነት፥ ከግብ አልባነትና ከስጋት የምንወጣበትን መንገድ ያሳያል። የወንጌሉንም ምንነት የሚዳስስ ግልጽ ክለሳ እንደሚከተለው ቀርቧል። (ፍላጎት ላላቸው አንባቢያን የሙሉውን ወንጌል አንድ ቅጂ በደስታ እንሰጣለን)

እንግዲህ ወንጌሉ ምንድን ነው?

ይህን ጥያቄ ለመመለስ በርካታ ጥራዝ ያላቸው ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል። ዋና ዋናዎቹን ጥያቄዎች ቀጥለን እንመለከታለን። ከዚያም በኋላ እርስዎ ራስዎ እንዲያነቡና እንዲያጠኑ ይጠበቅቦታል።

«ወንጌል ማለት (የምሥራች) ማለት ነው። በዓለም ውስጥ ብዙ ዓይነት የምሥራቾች አሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን መልእክቱ ራሱ (የምሥራች) ነው ማለት ነው። እግዚአብሔር ሰውን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ መንገድ ከፍቷል። ይህም ከሰው ልጅ ጅማሬ ጀምሮ ደረጃ በደረጃ የተዘጋጀ የማስታረቅ መንገድ ነው። ቀጥለን እስኪ በመጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ ከተጠቀሱት ሰዎች የአንዳንዶቹን ምሣሌነት እንመልከት።

ሰው በመጀመሪያ በሰላምና በእግዚአብሔር ጋር ስምም በሆን ኑሮ ይኖር ነበር። ከዚያም የሐጢአት ውድቀት መጣ። አዳም (በዕብራይስጥ «ሰው» ማለት ነው) እና ሔዋን በራሳቸው ፍላጎትና ስሜት ተገፋፍተውና በሰይጣን «ተመርተው» የራሳቸውን ፈቃድ አደረጉ። እንደአምላክም ለመሆን ተመኙ አለመታዘዛቸውም በጌታቸው ላይ እንዲያምፁ አደረጋቸው። በውጤቱም ከዔደን ገነት ተባረሩ። ልጆቻቸውም የቤተሰቦቻቸውን ምሳሌ በመውረስ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ የሚኖር

ሰው የሚያጋጥመውን የተበላሸ ሕይወት ኖሩ። ከእነርሱም አንዱ የገዛ ወንድሙን ገድሎታል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለ ሰው ልጅ ዓመፅና ጥፋት እናነባለን። ከመጀመሪያው ውድቀት በኋላ ሁላችንም በውስጣችን ሆኖ ወደ ኃጢአት ከሚገፋፋን ኃይል ጋር ተፈጥረናል። ማንም ሰው ለማንኛውም ዓይነት ክፉ ባሕርይ መመሪያ አላስፈለገውም። ሁሉም ሰው ለክፉ ሥራ የሚሆን በቂ ችሎታ ይዞ ይወለዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንዲህ ሲል ያብራራል።

> «እግዚአብሐርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁልጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደሆነ አየ።»
>
> (ዘፍጥረት 6:5)

የሰው ልጅ ግን ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔርን ፍርድ የተጋነነ-የማይገባም አድርጎ በመቁጠር ያቃልለዋል። በራሳቸው ጥረት እየተማመኑ በማይሆን ተስፋ ላይ መደገፍን ይመርጣሉ። እግዚአብሔር ግን የዚህ ዓይነቱን አመለካከት አልደገፈውም።

> «ሕግ (የእግዚአብሔር ትዕዛዝ) መንፈሳዊ እንደሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ (በላቲን ‹ካርኒስ› ማለት ‹ሥጋ› ማለት ስለሆነ፥ ሥጋዊ አስተሳሰብ ማለት

> ነው» የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን አደርጋለሁና፥ ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም። በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፥ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። «እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ስወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ። በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ።»
>
> (ሮሜ 7፡14-23)

ታማኝና አስተዋይ የሆነ ሰው ሁሉ የዚህን ዓረፍተ ነገር እውነታ እንደሚቀበል ይገመታል። እንዲሁም ወደ ፈውስ የሚያመራው የመጀመሪያው መወጣጫ እርከንም ይኸንኑ ማስተዋል ነው። ከሁሉ የከፋ መታለል የሚመጣው ግን ራሳችንን ከሌሎች ሰዎች ጋር በማወዳደር ከሰዎች ሁሉ የከፋን እንዳልሆንን ለራሳችን በምንበይንበት ጊዜ ነው። ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ፊት የራሳችንን ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ ምናልባት በሃይማኖታዊ «ሥርዓቶች» እና በ «ደግ ሥራዎች» ለማካካስ እንሞክር ይሆናል። ራሳችንም ኃጢአታችንን

ለመፋቅ የምንችል ይመስለናል። ይህም የሚያዋጣ መንገድ አይደለም።

ታላቁ የውሃ ጥፋት የእግዚአብሔር ፍርድ ነበር። በዚህም ኖኅና የቅርብ ቤተሰቡ ብቻ

> «በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ። ኖኅም በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበረ፤ ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ»
>
> (ዘፍጥረት 6፡8፥9)

እንግዲህ የጽድቁ ባሕርይ ምን ይመስል ነበር? ከኃጢአታቸው መተባበርን በመተው፥ በእግዚአብሔር ቃል ላይ መደገፉ ነው፤ እምነት ማለትም ይኸው ነው።

የሚያሳዝነው ግን፥ የኖኅ ዘሮች ከጥፋት ውኃ በፊት ከነበሩት ሰዎች አለመሻላቸው ነው። እቅዳቸውንም አውጥተው እንዲህ አሉ፡-

> «ኑ፥ ጡብ እንሥራ በእሳትም እንተኩሰው ተባባሉ። ጡቡም እንደ ድንጋይ ሆነላቸው፤ የምድርም ዝፍት እንደ ጭቃ ሆነችላቸው። እንዲሁም ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው።»
>
> (ዘፍ.11፡3-4)

ጡብን በእሳት መተኮሱ ለምን አስፈለገ? ውኃን እንዳያስገባና እንዲጠነክር ነው። ለማጣበቂያ ዝፍትን(ቅጥራን) መጠቀም ለምን አስፈለገ? ምናልባት ከሸክላ በላይ ባያጠነክረውም አሁንም ውኃ ላለማስገባት ይረዳል። ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለመሥራት ለምን ያስፈልጋል? አንዱ ምክንያት በመጽሐፍ ላይ ተጠቅሷል:-

«ስማችንን እናስጠራው»

እግዚአብሔር ለባሪያው ለአብርሃም የተናገረው የሚከተለው ቃል አስደሳች ነው:-

«ስምህንም አከብረዋለሁ...» (ዘፍ.12፡2)

እግዚአብሔር ስላከበረው የአብርሃም ስም ታላቅና ባለዋጋም ነው። ዳሩ ለራሳቸው ስምና ዝና ለማስቀረት የፈለጉትን ሰዎች ስም ማን ግምት ይሰጠዋል! ግንቡን ለመገንባት ሌላም የተደበቀ ምክንያት ነበራቸው። ይኸውም፥ ከዓመፃቸው የተነሣ እግዚአብሔር ምድርን በሌላ የውሃ ማጥለቅለቅ እንደሚቀጣ ሳይገምቱ አልቀሩም። ስለዚህም ምናልባት የፈሩት ማጥለቅለቅ ቢደርስ ከግንቡ ጫፍ ላይ ይወጣሉ፤ ከዚያም ጎርፉን ዝቅዝቅ እያዩ ለማሳለፍ አስተማማኝ ማምለጫ እንዲሆናቸው ነበር፤ ለማለትም ይቻላል።

ያ ነበር እነርሱ ያሰቡት። ነገር ግን ጫፉ እስከሰማይ የሚደርሰው ግንባቸው በተሠራ ጊዜ የሚከተለውን ውስጠ ወይራ አባባል እናነባለን።

«እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ»

(ዘፍ.11፡5)

ከዚያም በኋላ ሰው ከእግዚአብሔር ፍርድ ለማምለጥ «ግንቦች» ለመሥራት ሲሞክር ቆይቷል። የፍልስፍና፥ የፖለቲካ፥ ከሁሉም በላይ ደግሞ የሃይማኖት «ግንቦችን»። እነዚህ እንደ እግዚአብሔር ሕግና ፈቃድ ለመኖር ባለመቻላችን ሊመጣብን ካለው ፍርድ ከልሱ የተስፋ ጨረር የሚሰጡን የሃይማኖት መንገዶች ናቸው። ሕጉም ከእርሱ ጋር ለመኖር እንድንችል ልንቀበለው የሚገባ ቅድመ ሁኔታ ነው።

«እኔ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ!
በፊቴ ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ!
የተቀረጸውንምስልለአንተአታድርግ!
የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ!

ከዚህ ላይ የተጨመሩት በሰዎች መካከል ለሚኖረው ግንኙነት የሚጠቅሙ ሕጎች ናቸው:-

«እናትህንና አባትህን አክብር፤ አትግደል፤ አታመንዝር፤» (ዘጸአት 20፡1-17)

የመጨረሻው ክፍል በአዲስ ኪዳን እንደሚከተለው ተጽፏል፡-

> «ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው»
> (ሮሜ 10፡13)

እንዲህ ዓይነት ፍቅር ያለው ሰው (ወይም ያላት ሴት) የት አለ?

መልካም፥ «አፈቅርሃለሁ! (አፈቅርሻለሁ!)» እንላለን። ይህን ስንል ግን «አንተን (አንቺን) ለራሴ እፈልጋለሁ» ማለታችን ነው።

አብራም፥ ወይም በኋላ እንደተጠራው አብርሃም እንደዚህ ባለ ማኅበረሰብ ውስጥ ኖሯል። እግዚአብሔር ከቤተሰቡና ሃይማኖታዊ ከሆነ አካባቢው ሲጠራው ታዝዞአል። አብርሃም በምንም ዓይነት ፍጹም ሰው አልነበረም(ዘፍ.12፡10-20፤ 15፡1-6 ከ 16፡1-4፤ 17፡15-19፤ 20፡1-11 ወዘተ ጋር አንብብ።)፤ ነገር ግን «አብራምም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት።» (ዘፍ.15፡6) አብርሃም የእግዚአብሔርን ቃል አመነ ከእግዚአብሔርም ቃል ኪዳን ጋር ተጣበቀ። በሒሳብ ማወራረጃ መዝገብ ውስጥ የገቢና የወጪ መመዝገቢያ ቅጽ እንዳለ ሁሉ ለእያንዳንዱም ሰው ሕይወት የተዘጋጀ መዝገብ አለ። ኃጢአት ሁሉ አንድን

ሰው ወይም ነገር ከእግዚአብሔር በላይ መውደድ ቢሆን ወይንም ሌላውን ሰው ከራስ በታች መውደድ (በዚህ ላይ ትንሽ ልናስብበት ይገባል) በአሳብ፥ በቃልም ሆነ በተግባር የፈጸምነው በደል ሁሉ በመጽሐፍ ይጻፍብናል። መልካም ሥራችንም እንዲሁ ተመዝግቧል! ዳሩ ግን መልካም ሥራዎች ከየት ይመጡልን ይሆን? ይኼ ምናልባት አሳዛኝ ዜና ሊሆን ይችላል። መልካም ሥራዎችን ማከናወን ኃላፊነታችን ነው። እኛው ነን የምንሰራቸው ኢየሱስ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሏል፡-

> «...የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፤ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ።»
> ሉቃስ 17፡10

ስለ አብርሃም የሚከተለውን ከሌላ ቦታ ላይ እናነባለን፡-

> «እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደነበረ፥ በሥራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን?»
> (ያዕቆብ 2፡22)

ደግ ሥራዎች ለኃጢአት ይቅርታ እንደማይበቁ እርግጥ ነው። ዳሩ ግን የሚያስደስተው ነገር የአብርሃም እምነት በገቢ መመዝገቢያ ቅጽ ላይ መመዝገቡ ነው፡-

«አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት» እግዚአብሔር ከራሱ ዘንድ የሆነውን የሕይወት መሠረትና ከአለመታዘዝ በኋላ የሚገልጸውን የማስታረቅ ደንብ በአብርሃምና በዘሮቹ በኩል ለሰው ልጅ ለማሳወቅ ፈለገ።

በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሳንታዘዝ ስንቀር በእግዚአብሔር ላይ ጦርነት እናውጃለን። ዓመፀኞችም እንሆናለን። እግዚአብሔር ግን ሰላምን እንካችሁ ይለናል! እስራኤል ከሰውና ከአጋንንቶች መታለል የተነሳ በሃይማኖት ጽልመት ውስጥ ለሚቅበዘበዘው የዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔርን መልካም ዜናና እቅድ እንዲያመጡ ይጠበቅባቸው ነበር። ዳሩ ግን እስራኤል የአብርሃምን አምላክ «በመዘንጋት» ሃይማኖታዊ ቢሆንም እንኳ ከእግዚአብሔር ሀሳብ የተነጠለ (የማይስማማ) ኑሮ መኖር ጀመሩ።

እንደገና ጣልቃ በመግባት እግዚአብሔርም ሙሴን በሰደደ ጊዜ በግብጻውያን ባርነት ሥር የሚኖሩትን እስራኤላውያን እግዚአአብሔር ታላላቅ ምልክቶችና ድንቆች አድርጎ ነጻ አወጣቸው። ከዚያ በኋላ በመካከላቸው ስለ እግዚአብሔር ግርማና ኃይል የማያውቅ ማንም አልነበረም። እግዚአብሔርም ከእስራኤል ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ይህም ዛሬ «ብሉይ ኪዳን» ተብሎ የሚጠራው ነው። እስራኤል ሁሉ አዲስ

የሕይወት መንገድ እንዲከተሉ እግዚአብሔር አዘዘ። ታላቅ ትዕዛዙንም ሲሰጥ እንዲህ አለ፡-

> «...ዛሬ በፊትህ ሕይወትንና መልካምነትን፥ ሞትንና ክፋትን አኑሬአለሁ። በሕይወትም እንድትኖር እንድትበዛም አምላክህም እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር እንዲባርክህ አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ፥ በመንገዱም ትሄድ ዘንድ ትዕዛዙንና ሥርዓቱንም ትጠብቅ ዘንድ ዛሬ እኔ አዝዝሃለሁ። ልብህ ግን ቢስት፥ አንተም ባትሰማ፥ ብትታለልም፥ ለሌሎችም አማልእክት ብትሰግድ፥ ብታመልካቸውም፥ ፈጽማችሁ እንድትጠፉ እኔ ዛሬ እነግራችኋለሁ፤ ዮርዳኖስን ተሻግረህ ትወርሳት ዘንድ በምትገባበት ምድር ዘመናችሁን አታስረዝሙም። በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤ እግዚአብሔር ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም እርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወደው ትጠባበቀውም፥ ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ።» (ዘዳግም 30፡15-20)

ነገር ግን ሰው ከትዕዛዛቱ አንዱን ቢተላለፍ ምን ይሆናል? ይጠፋ ይሆን?

«ነገር ግን መጽሐፍ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ፥ ኃጢአትን ትሠራላችሁ ሕግም እንደተላላፊዎች ይወቅሳችኋል። ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ «አትግደል» ብሎአልና፤ ባታመነዝር ነገር ግን ብትገድል ሕግን ተላላፊ ሆነሃል።»

(ያዕቆብ 2፡8-11)

«ከአገሩም ሕዝብ አንድ ሰው ኃጢአት ሳያውቅ ቢሠራ፥ እግዚአብሔርም አትሥራ ያለውን ትዕዛዝ ቢተላለፍ፥ ቢበድልም፥ ለእርሱም የሠራው ኃጢአት ቢታወቀው፥ ስለሠራው ኃጢአት ነውር የሌለበትን እንስት ፍየል ለቁርባኑ ያመጣል። እጁንም በኃጢአት መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል፥ የሚቃጠልም መሥዋዕት በሚታረድለት ሥፍራ የኃጢአትን መሥዋዕት ያርዳል። ካህኑም ከደምዋ ወስዶ... ከመሠዊያው በታች ያፈስሰዋል።... ካኑም በእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል። ስለ እርሱም ያስተሰርያል፥ እርሱም ይቅር ይባላል።»

(ዘሌዋውያን 4፡27-31)

ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ቢተላለፍና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እርቅን ለማድረግ ባይወድ ይጠፋል! እግዚአብሔር ግን ይህን የጭካኔ መንገድ ማለትም መሥዋዕት ለምን መረጠ? የኃጢአትን አስከፊነት በሕዝቡ ዘንድ ለማስረገጥ ስለፈለገ ይመስለኛል፥ የምትወደውንና የምታሳድገውን ለማዳ እንስሳ በሚቀጥለው ጊዜ ለምትሠራው ኃጢአት ማረድና ማቃጠል! ይህን ላለማድረግ ፍጹም የሆነ ራስህን የመግዛት ልምምድ እንደምታደርግ ጥርጥር የለውም።

እግዚአብሔር የገዛ ሕዝቡን ራሳቸውን እንዲጠብቁና ለእርሱ ብቻ እንዲኖሩ ፈለገ። ዳሩ ግን ሰዎቹ ማጉረምረምና ዓመፃን አደረጉ። በመጨረሻም በባዕድ አምልኮት በመጠመድ በጨለማ ውስጥ ተዘፈቁ። እግዚአብሔርን ከአዲስ የሕይወት ሥርዓቱ ጋር መተው ብቻ ሳይሆን እረሱት።

የእግዚአብሔር ማስጠንቀቂያዎች ሁሉ እውን ሆኑ፤ እስራኤላውያን በሽንፈት ለመኖር ተገደዱ። በመጨረሻም በዓለም ሁሉ ተበተኑ ለብዙ መቶ ዓመታትም በከባድ ስደት ውስጥ በማለፍ ተሰቃዩ፤

የእግዚአብሔርም የትንቢት ቃል አንድም ሳይቀር ተፈጸመባቸው።

ካለመታዘዝ የተነሳ የተመረጠው የእስራኤል ሕዝብ ወደ ጎን ተተወ። «ብሉይ ኪዳኑንም» አፈረሱት። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር እቅዱን ከሰው ልጅ ጋር ማድረግ ቀጠለ። ድሮውኑ ለአዳምና ለሔዋን ከዘራቸው አንድ ሰው እንደሚመጣና የሰይጣንን ራስ እንደሚቀጠቅጥ ነግሮአቸው ነበር። ይህም የሚመጣው ሰው ከአብርሃም ትውልድ መሆን ነበረበት፡-

> «...የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ»
> (ዘፍጥረት 12፡3)

> «...በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃልና ተብሎ እንደተጻፈ።»
> (ዘፍጥረት 21፡12)

አይሁዶች ይህን የሚጠበቀውን ነጻ አውጪ መሢሕ ይሉታል(ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ ንጉሥ ካህን ወይም ገዢ ማለታቸው ነው) ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት የዘር ሐረግ እንደሚመጣም እግዚአብሔር ተናግሯል፡-

> «ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፤ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ፥ ዘርህን ለዘላለም

> አዘጋጃለሁ፤ ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ»

> «እኔም ደግሞ በኵሬ አደርገዋለሁ፤ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል። ለዘላለምም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ፥ ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው። ...ዙፋኑንም እንደሰማይ ዘመን አደርጋለሁ... ዳዊትን እንዳልዋሸው አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ። እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ፤ አይጸጸትምም፥ እንዲህ ብሎ፡- ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ። ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና፤ አለቅነቱም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ‹ድንቅ መካር›፥ ‹ኃያል አምላክ›፥ ‹የዘላለም አባት›፥ ‹የሰላም አለቃ› ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያጸናውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል፤ ለሰላሙም ፍጻሜ የለውም።» (መዝ.(89)፡3-4፤ 27-35፤ 132፡11፤ ኢሳይያስ 9፡6-7)

የዳዊት ምድራዊ ዙፋኑ የተተካው በገዛ ልጁ ነበር። ዳሩ ግን ያ መንግሥት ከወደመ ብዙ ዘመን ሆኖታል፤ ተረስቷልም። እግዚአብሔር የሚናገረው ስለዘላለማዊ ዙፋን ስለሆነ ከዚህ ስለሚበልጥ ትልቅ ነገር እየተናገረ መሆን አለበት። ዘላለማዊ ሊሆን የሚችል የሰው

መንግሥት ደግሞ የለም። ነቢዩ የተነበየለት ይህ ሰው (ከድንግል የተወለደው፤ ኢሳይያስ 7፡14) ማን ሊሆን ይችላል? እርሱማ መሢሁ ኢየሱስ ነው። እርሱ እንዴት ኃያል አምላክ የሰላም አለቃ ሊሆን ይችላል? መልሱን ለእግዚአብሔር መተው ይኖርብናል። ነገር ግን ይህ ሰላም የት አለ? ተስፋ የተሰጠው ፍትህና ጽድቅስ ወዴት አለ? መንግሥቱስ ራሱ የት አለ? ኢየሱስ እነዚህን ጥያቄዎች በዚህ ዓይነት መልሶአቸዋል፡-

> «የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤ ደግሞም ‹እነኋት በዚህ ወይም እነኋት በዚያ አይሉአትም› እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና።»
>
> (ሉቃስ 17፡20-21)

እነዚያ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም አላቸው። ይቅር ተብለውና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ጽድቅን አግኝተዋል።

> «...በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ...»
>
> (ፊልጵስዩስ 3፡9)

ኢየሱስ በተወለደ ጊዜ ወደ እርሱ የሚያመለክቱትን ብዙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፈጽሞአል። እርሱ

የእግዚአብሔርን መንግሥት መስርቷል። እግዚአብሔርም በእርሱ ራሱን ለሰው ገልጦአል። ኢየሱስ በአንክሮ በሚከታተለው ዓለም ፊት ያለኃጢአት በንጽሕና ኖረ። በአኗኗሩም የሰው ልጆች ሁሉ እንድንኖር የሚፈልገውን ሕይወት አሳየ። በኋላም እያንዳንዱን ሰው ከእግዚአብሔር አባቱ ጋር ለማስታረቅ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ የመስቀልን ሞት ተቀበለ።

> «ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ።»
>
> (1ኛጴጥ.2፡24)

«የምሥራች» ወይም ‹ወንጌል› ማለት ይህ ነው። ከዚህ ውጭ ሰው የሚያደርገው ነገር የለውም ያለው አማራጭ ቢኖር ራሱን ለኃጢአት በሰጠ እኔነት ትእዛዝ ሥር መኖር ብቻ ነው። ኢየሱስ እንደተተነበየለት ሁሉ በመጣ ጊዜ በደላችንንና ኃጢአታችንን በራሱ ላይ አደረገ። የኃጢአታችን ውጤት የሆነውን ሥቃይ ተሠቃየ። በአንተ ላይ ሊወድቅ የሚገባው ፍርድ በእርሱ ላይ ወደቀ። በመጨረሻም እንዲህ አለ፡-

> «መልካም እረኛ እኔ ነኝ... ነፍሴንም ስለበጎች አኖራለሁ... በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ፤ እኔም አውቃቸዋለሁ፤ ይከተሉኝማል፤ እኔም የዘላለም

ሕይወት እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘላለምም አይጠፉም፤ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።»
(ዮሐንስ 10፡14፥15፥27፥28)

ያ ነው እንግዲህ የምሥራቹ፥ አንተ ለማድረግ የማትችለው ሁሉ ለአንተ ተደርጎልሀል። አሁን በቀረው ሕይወትህ አዳኝህ የሆነውን እግዚአብሔርን እያመሰገንህ ለመኖር ትችላለህ(ኢሳይያስ 63፡7-11) ሕይወትህ የእርሱ ሆኗል፤ ስለሆነም ጠፍቶ እንደተገኘው በግ ድምጹን ሰምተህ በእምነት ተከተለው። ለእነርሱ ሕይወቱን ቤዛ አድርጎ ስለከፈለ (ቤዛ የባሪያን ነጻነት ለመግዛት የሚከፈል ዋጋ ነው)።

የእርሱ የሆኑትን ያውቃቸዋል። የራሱ የሆኑትንም የዘላለም ሕይወት ይሰጣቸዋል። የምሥራቹ እንግዲህ ይኼ ነው!

ነገር ግን ኢየሱስ ሞቶ አልቀረም። ከሞት ተነሥቷል! እንደገና የምሥራች! ወደ ሰማይ አርጎ፥ «በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞም ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» (ሮሜ 8፡34)

አሁንም ተጨማሪ የምሥራች አለ! ወይስ ለአንተ መርዶ ይሆንን? ኢየሱስ እንደገና ይመጣል! ለእርሱ ለመስገድና ጉልበታቸውን በፊቱ ለማንበርከክ ባልፈለጉ ሰዎች ላይ በጽድቅ ለመፍረድ ይመጣል (ፊልጵስዩስ

2፡9፥10) ይቅርታን ላለመቀበል በተኩራሩትና እምቢተኛ በሆኑት ሰዎች ሁሉ ላይም ይፈርዳል። ነገር ግን በሥጋ የሞቱትንና ተስፋቸውንና እምነታቸውን በእርሱ ላይ የጣሉትን ለማስነሳት ይመጣል!

ይህ ሁሉ እንግዲህ የአዲስ ኪዳን ክፍል ነው። እርሱም በብሉይ ኪዳን የተተነበየ ነገር ነው፡-

«... አዲስ ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል... ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፤ እነርሱም በኪዳኔ አልጸኑምና... ከእነዚያ ወራት በኋላ ...የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና... ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑልኛል... በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።»
(ኤርምያስ 31፡31-34)

ጻድቁ ኢየሱስ ለኃጢአተኛው ሰው በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ፥ አዲስ ኪዳን ፍጻሜ አግኝቷል። ስለዚህም አሁን እግዚአብሔር ለኃጢአቱ ይቅርታ ያዘጋጀውን መንገድ ለመቀበል ለሚፈልጉ ሁሉ፥ መንገዱ ክፍትና አስተማማኝ ነው። ይህም የሚሆነው ፍርድን ለማወጅ እስኪመለስ ድረስ ነው።

ዳኑ ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለተቃወሙ፥ ወይም ሰው ሠራሽ ሃይማኖት ለመረጡ ሰዎች የምሥራቹ ምንም አይጠቅማቸውም። ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ወዲያውኑ ለመመሥረት ከቶ አይቻላቸውም። ምንም እንኳ ኢየሱስ ለሰው ልጅ ሁሉ ቢሞትም ማዳኑን የሚቀበሉት ግን ለይቅርታው ራሳቸውን እንደ ስጦታ ያቀረቡት ሰዎች ብቻ ናቸው። ስለሆነም እንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላምን ማድረግ የግል ኃላፊነት ነው ማለት ነው። ሁላችንም ይህን ለማድረግ ተጠርተናል፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ፡-

«እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ ለእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ፥ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን።»
(2ቆሮንቶስ 5፡19፥20)

ተብሎ እንደተጻፈ። በእርግጥ ወደ እግዚአብሔር እንድንመለስ ታዝዘናል፡-

«እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤ ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያውም ቀን ባዘጋጀው ሰው

እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለው፤ ...»
(የሐዋርያት ሥራ 17፡30፥31)

ስለሆነም ይቅር ለመባልና ተቀባይነት ለማግኘት ለዚህ ጥሪና ትዕዛዝ ምላሽ መስጠት አለብን።

ይህም የሚሆነው ሕይወትህን መዝነህ በውስጡ ያለውንም ኃጢአት ተረድተህ፥ ለእግዚአብሔር ስትናዘዝና በመጸጸት ከኃጢአትህ ለመመለስ ስትወስን ነው። እንዲሁም እንዲያነጻህ፥ እንዲቀበልህና የአንተም ጌታ እንዲሆን ኢየሱስን ስትጠይቀው ነው።

«ከእርሱም የሰማናት፥ ለእናንተም የምናወራላችሁ መልዕክት እግዚአብሔር ብርሃን ነው። ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።

«ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን፤ እውነትም አናደርግም፤ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፤ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ...ኃጢአት አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን፤ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።»
(1ኛዮሐ.1፡5-10)

ለዚህ ምላሽ በመስጠት እግዚአብሔር ራሱ እንዲህ ብሏል፡-

«...በደላቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና»

(ኤርምያስ 31፡34)

ከኃጢአታችን ሊያድነን የሚችለው መሥዋዕት የሆነልን ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ፥ ኢየሱስን እንደ አዳኛችንና እንደ ደኅንነታችን ምንጭ አድርገን እንቀበለዋለን። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር የጠለቀ አንድነት ሊመሠርት ላለው ሕይወት የመጀመሪያ ደረጃ ነው።

አሁን ንጹሕ ሆነሃል። የሕይወትና የልብህም እድፈት ተወግዷል። አሁን ያንተ ልብ በአዳዲስ ነገሮች ከሁሉም በፊት ደግሞ በራሱ በእግዚአብሔር ሀሳብ መሙላት አለበት። ራሱን በሕይወትህ ዙፋን ላይ እንዲያስቀምጥና በልብህ ውስጥ እንዲያርፍ መፍቀድና በጸሎት መጋበዝ ያስፈልጋል። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ሕይወትህን ማደስ ይጀምራል። ፈቃድህንም ለፈቃዱ ያስገዛል።

«በሕይወትም ያሉት ስለእነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ስለሁሉ ሞተ»

«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል። ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ

ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው።»

(2ኛቆሮ.5፡15፥17፥18)

ይህን ያደረገ ሰው የእግዚአብሔር ንብረት ወደ መሆን ይቀየራል። እርሱም በእግዚአብሔር የመለኪያ መሥፈርት መሠረት ተቀባይነትን አግኝቷል። ይቅርም ተብሏል። እንደገናም ያንን አዲስ ሕይወት ለመምራት አዲስ ዓይነት ሥልጣንና ምሪት ከእግዚአብሔር ቃል ይቀበላል። ይኸውም ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሆንና በምድርም ላይ የእርሱን መንግሥት ለመመሥረት ነው። ይህ ደግሞ ወደ ውብ ሕይወትና ቅድስና ይመራል፥ ሚዛን የጠበቀ ነቀፋም የሌለበት ሕይወት ማለት ነው። በዚህም ጊዜ ወደ መጀመሪያው የሕይወት ትርጉምና ዓላማ ተመልሰናል ማለት ነው። መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን በፍጥረተ ዓለም የተሰጠንን ነገር ሁሉ ዕለት በዕለት መለማመድ በሚቻልበት በእግዚአብሔር ሁለንተናዊ ሙላት ሕይወት እንኖራለን። ምናልባት ከሁሉም የሚበልጠው የመጨረሻ ዕጣዬን ማወቅ መቻሌ ላይ ነው። ከእንግዲህ ስለወደፊት በተለይም ስለሞት መፍራት አያስፈልገኝም። ምክንያቱም ኃጢአቶቼ በእግዚአብሔር ዘንድ ተረስተዋል። እርሱም እንዲህ ነው የሚለው፡-

«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።» (ሮሜ 8፡1)

በጥፋት ውሃ ጊዜ ኖኅና ቤተሰቡ በመርከብ ውስጥ ሆነው እንደዳኑ ሁሉ በ ‹ኢየሱስ› ያሉትም እንዲሁ ከሚመጣው የእግዚአብሔር ቁጣ የተጠበቁ ናቸው። የሁላችንም ኃጢአት በኢየሱስ በኩል ስለተቀጣ የእግዚአብሔርም ፍርድ ተፈጽሞአል።

ይህም አዲስ ሕይወት አዲስ ፍላጎትን ያመጣል፡-

በመጀመሪያ ደረጃ ራስን በመስጠትና በፍቅር በመታዘዝ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሕይወት መኖር።

ሁለተኛ፥ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር ኅብረት ለማድረግ መፈለግ። እና ሦስተኛ ይህን አዲስ ሕይወትና ተስፋ ለሌሎች ማካፈል። የዚህችም መጽሐፍ ዋና ዓላማ ይኸው ነው።

ስለዚህ ይህን ሕይወት አመንትተህ እንዳትተው እንጋብዝሃለን፤ ነገር ግን ለተጨማሪ መረጃዎች፥ ወይም በዚህች መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ በማናቸውም ርዕሶች ላይ ማንኛውም ጥያቄ ቢኖርህ ከምትፈልገው በላይ እንድትገፋ ሳትገደድ ለነጻና ግልጽ ውይይት ወደ እኛ እንድትጽፍ ግን እንጠይቃለን። በጠንቃቃነታችንና ኃላፊነታችንን በሚገባ በመወጣታችን ላይ እርግጠኛ ልትሆን ትችላለህ።

ለእኛ ለመጻፍ ከፈለግህ እባክህ ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ጻፍልን።

አድራሻችን የሚከተለው ነው፡-

የሕይወት በር
የፖ.ሣ.ቁ. 4937
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ